# የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሙላቱ ተሾመ ለሁለቱ ምክር ቤቶች ያቀረቡት ንግግር



**የተከበራችሁ የህዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች አባላት፣**

**የተከበራችሁ መላ የአገራችን ህዝቦች፣**

**ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶችና ክቡራትና ክቡራን፤**

ከሁሉ በማስቀደም ሁለቱ ምክር ቤቶች በ5ኛው የስራ ዘመናችሁ፣ ሁለተኛውን ዓመት ለምትጀምሩበት ለዛሬው ቀን በመብቃታችን የተሰማኝን ልባዊ ደስታ በራሴና በኢፌዴሪ መንግስት ስም ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡ በዚህም አጋጣሚ በአገራችን ልዩ ልዩ አካባቢዎች በተካሄዱ ግጭቶች በህይወትም ሆነ በአካል ለተጎዱ ወገኖቻችን፣ እንዲሁም በቅርቡ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልል የኢሬቻ ባህላዊ ስነ-ስርዓትን ለማክበር ከተሰበሰቡ ወገኖቻችን መካከል ፀረ ሰላም ኃይሎች በፈጠሩት ግርግር ህይወታቸው ላለፈ ወገኖችና ቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ለመላው የኦሮሞና የአገራችን ህዝቦች የተሰማኝን ጥልቅ ሃዘን በራሴና በመንግስት ስም ለመግለፅ እወዳለሁ፡፡

**የተከበራችሁ የህዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች አባላት፣**

**የተከበራችሁ መላ የአገራችን ህዝቦች፤**

በፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ስርዓታችን ወሳኝ ሚና የሚጫወቱትን ሁለቱን ምክር ቤቶች በምንከፍትበት በዛሬው እለት፣ በብዙ መሰረታዊ ጉዳዮች ዙሪያ መምከር እንደሚገባን ከማንም የተሰወረ አይደለም፡፡ ያሳለፍነው ዓመት አገራችን ኢትዮጵያ በብዙ መስኮች ወደፊት የተራመደችበት እንደሆነው ሁሉ ልዩ ልዩ ሁኔታዎች የተከሰቱበትም ነበር፡፡ በመሆኑም መልካም ጅምሮችን አጠናክረን ለማስቀጠል፣ ችግሮቻችንን ደግሞ መላ የአገራችንን ህዝቦች በሚያረካ ደረጃ ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ እነዚህን ሁኔታዎች አንስተን በዝርዝር ልንመክርባቸው ይገባናል፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ ለበርካታ ዓመታት በፈጣን የለውጥ ሂደት ወደፊት ስትራመድ ቆይታለች፡፡ ለማንም ግልፅ እንደሚሆነው ለውጡ ከገጠር እስከ ከተማ፣ በሁሉም የህይወት መስክ የተካሄደ ከመሆኑም በላይ ያልዳሰሰው የህብረተሰብ ክፍልም የለም፡፡ ለውጡ በዚህ ብቻ ሳይወሰን በህብረተሰባችን ውስጥ መሰረተ ሰፊ የለውጥና የተጠቃሚነት ጥያቄዎች ለመቀስቀስ ምክንያት ሆኗል፡፡ ከሰራናቸው መልካምና ውጤታማ ተግባራትም ሆነ ከታዩ ድክመቶችና ከተከሰቱ ተጨባጭ ችግሮች በመነሳት፣ ቀጣዩ ሂደት ይበልጥ ፍሬያማና የህዝባችንን መብትና ተጠቃሚነት ይበልጥ የሚያረጋግጥ፣ የአገራችንን ሰላምና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ የሚያጠናክር እንዲሆን አድርጐ መቃኘት እጅግ አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝበት ወቅት ላይ ደርሰናል፡፡ በመሆኑም ባሳለፍነው ዓመት ካሳካናቸው ውጤቶችም ሆነ ካጋጠሙን ችግሮች በመነሳት ጉዳዮን በዝርዝር መመልከትና ቀጣዮቹን አቅጣጫዎች በትክክል መተለምና በላቀ ርብርብ ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡

ባሳለፍነው ዓመት አገራችንን ከገጠሟት ችግሮች መካከል አንዱና ትልቁ ሰፊ መልክዓ ምድርን የሸፈነው የድርቅ አደጋ ነበር፡፡ ድርቁ በዓለም አቀፍ ደረጃ የታየውን የተፈጥሮ መዛባት ተከትሎ የተከሰተ ሲሆን በአስከፊነቱም ባለፉት 50 ዓመታት ከታዩ ድርቆች ሁሉ የሚስተካከለው አልነበረም፡፡ በዚህ የተነሳ በብዙ ሚሊየኖች የሚቆጠሩ አርሶ አደሮችና ቤተሰቦቻቸው ለረሃብ አደጋ የሚጋለጡበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡ የድርቁ አስከፊነት በእንስሳት ሀብታችንም ላይ ከባድ የመኖና የውሃ እጥረት ችግር እንዲያጋጥም በማድረጉ የገጠሩ ህብረተሰባችን ህይወት አደጋ ላይ ወድቆ ነበር፡፡

ችግሩ ከተከሰተበት ወቅት ጀምሮ ይህ አደጋ መከሰቱን የተገነዘበው የኢፌዴሪ መንግስት፣ ከመቸውም ጊዜ በተሻለ ደረጃ በራሳችን አገራዊ አቅም በመተማመን ልንፈታው እንደምንችልና እንደሚገባን በመተማመን ተንቀሳቅሷል፡፡ በተወሰነ ደረጃ ችግሩ ከአገራችን አቅም በላይ ሆኖ ቢገኝ በወገኖቻችን ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለማስወገድ ይቻል ዘንድ በወቅቱ ለዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ከማሳወቅ ሳይቆጠብ፣ ችግሩን በወሳኝነት በራሳችን አቅም ለመፍታት ተንቀሳቅሷል፡፡ በዚህ መሰረት አደጋውን ለመቋቋም የሚያስችለን በጀት በመመደብ፣ በአንድ በኩል ከአገር ውስጥ ትርፍ አምራች አካባቢዎች እህል በመግዛት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በድርቅ ለተጠቁ ወገኖቻችን የሚሆን ቀለብ ለማቅረብ የሚያስችል ከዓለም ገበያ የእህል ግዥ አካሂዷል፡፡ የተገዛው እህል ከማንኛውም ሸቀጥና ምርት ቀድሞ እንዲጓጓዝና ለተረጅዎቹ እንዲደርስ ማድረግም ተችሏል፡፡ በውጤቱም ከድርቁ ጋር የተያያዘ ማንኛውም አይነት ሰብዓዊ ቀውስና ጉዳትን ለማስወገድ ችሏል፡፡ ከዚህ የተሳካ እንቅስቃሴ ጐን ለጐን ለእንስሳት መኖና ውሃ ለማቅረብ የተሳካ እንቅስቃሴ አካሂዷል፡፡ መንግስት በራሳችን አገራዊ አቅም በመተማመን ችግሩን ለመፍታት ያደረገው ይህ እንቅስቃሴ ዓለም አቀፍ ለጋሽ አገሮች በተለመደ የትብብር መንፈስ ከሰጡት እርዳታ ጋር ተዳምሮ የድርቁ አደጋ በዜጐች ላይ ይህ ነው የሚባል ጉዳት ሳያደርስ እንድናልፍ አስችሏል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ይህን በመሰለው የተፈጥሮ አደጋ ወቅት ከጎናችን ሳይለይ የእርዳታ እጁን በመዘርጋት የምናውቀው ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ፣ ዘንድሮም ላደረገልን ቀና ትብብር በራሴና በኢፌዴሪ መንግስት ስም ላመሰግን እወዳለሁ፡፡

ባለፈው ሩብ ምእተ ዓመት ያጋጠሙንን የድርቅ አደጋዎች ከመቋቋም አኳያ ተመሳሳይ ጉዳትን ስናስወግድ መቆየታችን ከመላ የአገራችን ህዝቦች የተሰወረ አይደለም፡፡ በመሆኑም ይህን የመሰለ ውጤት ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘ ነው ሊባል አይችልም፡፡ ይህም ሆኖ የዘንድሮውን ውጤት ከዚህ ቀደም ከነበሩት ድርቅን የመከላከል እንቅስቃሴዎች የሚለየው በወሳኝነት በራሳችን አገራዊ አቅም በመተማመን የፈታነው መሆኑ ነው፡፡ ልዩነቱ አገራችን ኢትዮጵያ ባለፉት 25 ዓመታት ባስመዘገበችው የኢኮኖሚ እድገትና በፈጠረችው አገራዊ የመቋቋም አቅም፣ በድርቅ የመጠቃት አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ ከማንም እርዳታ ሳንጠብቅ ችግሩን በራሳችን አቅም ለመፍታት እንደምንችል የተረጋገጠበት መሆኑ ነው፡፡ ይህ የመላ የአገራችን ህዝቦች የትግልና ልማታዊ ርብርብ ውጤት በመሆኑ መላ ኢትዮጵያዊያን በዚህ ታላቅ አገራዊ ድል ልባዊ ኩራት ሊሰማን ይገባል ብየ አምናለሁ፡፡ በገጠር የተፈጥሮ ሃብት ልማት ስራዎች በተከናወኑባቸው አካባቢዎች የከርሰ ምድር ውሃ ይዞታችን እንደበለፀገና በተጨባጭ ለክፉ ቀን ስንቅ ሆኖ እንዳገለገለን ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም ባለፈው ዓመት በዝናብ እጥረት ያጋጠመን የምርት ቅናሽ በሌላ ጊዜ ከሚያጋጥመን ያነሰ እንደነበርም ታይቷል፡፡ በድርቅ በተጠቃንበት ዓመት ከመኸር ግብርና የተገኘው 26.7 ሚሊዮን ቶን የግብርና ምርት ከዚያ በፊት ከነበረው በመጠኑ የተሻለ መሆኑ ሲታይ የግብርና ልማት አቅጣጫችን ምን ያህል ትክክለኛ እንደሆነም አረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በዚሁ አጋጣሚ በዚህ መስክ የጀመርነውን መልካም ስራ ከመቸውም ጊዜ በላይ አጠናክረን ልንገፋበት እንደሚገባን ለማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡

በዘንድሮው ክረምት በሁሉም የአገራችን አካባቢዎች የተመጣጠነና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ በማግኘታችን፣ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ካለፈውም በጣም የተሻለ ምርት ለማግኘት በሚችሉበት ደረጃ ተንቀሳቅሰዋል፡፡ ተጨባጭ ውጤቱ ወደፊት የሚገመገም መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከእንግዲህ ሊያጋጥም የሚችል ማንኛውም ዓይነት ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ጉዳት እንዳያደርስ ተጠንቅቀን እስከተረባረብን ድረስ የ2008/09 የግብርና ምርታችን ከፍተኛ ጭማሪ የሚገኝበትና የህዝባችንን ተጠቃሚነት ይበልጥ የሚያጐለብት እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡

**የተከበራችሁ የህዝብ ተወካዮች እና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች አባላት፣**

**የተከበራችሁ መላ የአገራችን ህዝቦች፣**

ባሳለፍነው ዓመት ያጋጠመንን የድርቅ አደጋ ለመቋቋም ከፍተኛ ጥረት እያደረግን በነበረበት ወቅት፣ የተከሰተው ሌላው አገራዊ ችግር፣ በአንዳንድ የአገራችን አካባቢዎች ሁከትና ግጭት መቀስቀሱና አንፃራዊ የፖለቲካ አለመረጋጋት መታየቱ ነበር፡፡ ለሁላችንም ግልፅ እንደሚሆነው በልዩ ልዩ የአገራችን ክፍሎች፣ በተለይ ደግሞ ወጣቶች የተሳተፉባቸው ሁከቶችና ግጭቶች ተቀስቅሰዋል፡፡ በእነዚህ ግጭቶች ሳቢያ በአሳዛኝ ደረጃ የወጣቶችና ሌሎች ዜጎች፣ እንዲሁም የፀጥታ አስከባሪ ሃይሎቻችን ህይወት ተቀጥፏል፡፡ ቀላል የማይባል ንብረትም ወድሟል፡፡ በተጨማሪም የዜጎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ተስተጓጉሏል፡፡ በዚህ የተነሳ ደፋ ቀና ብለው ሰርተው ኑሮአቸውን ለማሸነፍ የሚንቀሳቀሱ ዜጎች ለፈተናዎች ተዳርገዋል፡፡ ይህን የመሰለው ችግር በየአካባቢው እንዲቀሰቀስ ምክንያት የሆኑ ወቅታዊ ችግሮች እንደነበሩ ባይካድም፣ ከተከሰተበት ሁኔታና ከደረሰው የህይወትና የንብረት ጉዳት በመነሳት መሰረታዊ ምክንያቶቹን በውል ማስቀመጥ ይገባል፡፡ እነዚህን ለመፍታት የሚያስችል የተሟላ የመፍትሔ ሃሳብ በማዘጋጀት መላውን ህብረተሰብ በሚያሳትፍ አግባብ ተግባራዊ ማድረግ ወሳኝ ሆኖም ተገኝቷል፡፡

ለማንም ግልፅ እንደሚሆነው ባሳለፍነው ዓመት በተከሰቱት ግጭቶች ውስጥ ዋነኛ ተዋናይ የነበሩት የአገራችን ወጣቶች ነበሩ፡፡ ይህ እውነታ ወጣቶቻችን የሚገኙበትን ሁኔታ በትክክል መገንዘብና ለችግራቸውና ለጥያቄያቸው የሚመጥን መሰረታዊ መፍትሔ ማቅረብ አጣዳፊ ሆኖ ይገኛል፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ በህዝብ ብዛት ከአፍሪካ በ2ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡ ወደ መቶ ሚሊዮን ከሚጠጋው ህዝቧ ውስጥ ደግሞ ከግማሽ የማያንሰው በወጣት የእድሜ ክልል የሚገኝ ነው፡፡ ስለሆነም በህብረተሰባችን ውስጥ የሚካሄድ ማንኛውም የለውጥ እንቅስቃሴ ተወደደም ተጠላም ወጣት ተኮር መሆኑ የግድ መሆኑ አይቀርም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አብዛኛው የአገራችን ህዝብ በገጠር የሚገኝ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ወጣቱም በዋነኛነት ተከማችቶ የቆየውና ዛሬም የሚገኘው በዚሁ የገጠሩ ክፍላችን ነው፡፡

ይህ የወጣት ኃይል ለረጅም ጊዜ በገጠር ተወስኖ ከቆየ በኋላ በተወሰኑ መሰረታዊ ምክንያቶች ከገጠር ወደ ከተሞች በመፍለስ ላይ ይገኛል፡፡ አብዛኛው የገጠር ወጣት መሬት አልባ በመሆኑ ከገጠሩ ጋር ተጣብቆ የሚቆይበት ጠንካራ ምክንያት የለውም፡፡ በዚህ ላይ የግብርና ምርታማነት እየጨመረ መሄዱን ተከትሎ፣ በመፈጠር ላይ ያለው ትርፍ ጉልበት ገጠርን እየለቀቀ ወደ ከተሞች እንዲንቀሳቀስ ግድ የሚልበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በተጨማሪም ወጣቱ በአገራችን የተስፋፋው የትምህርት እድል ተጠቃሚ ሆኖ ከቆየ በኋላ የወላጆቹን ልማዳዊ የግብርና ስራ ሊቀጥልበት የማይፈልግ እየሆነ በመምጣቱ የገጠሩ ወጣት ቀስ በቀስ ወደ ከተሞች በተለይ ደግሞ ወደገጠር ከተሞች እየጐረፈ መከማቸት ጀምሯል፡፡

ይህ ወጣት ገጠሩን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የለቀቀ ቢሆንም፣ በከተሞቻችን አስተማማኝ የስራና የገቢ ሁኔታ ገና ያልተፈጠረለት ነው፡፡ በተከማቸባቸው ከተሞች ሁሉ በአመዛኙ ከእለት ስራ ያለፈ ቋሚ የስራና የገቢ እድል የሌለው በመሆኑ ህይወቱ አስተማማኝ መሰረት ያልያዘ ነው፡፡ ሁኔታዎች ዘንበል ያሉ ቀን ለከፋ አደጋ እጋለጣለሁ ብሎ እርግጠኛነት በማጣት ውስጥ የሚገኝ ወጣት ነው፡፡ ይህን የመሰለው ወጣት በትንንሽ የገጠር ከተሞች ብቻ ሳይሆን፣ በትልልቅ ከተሞችም ጭምር የሚገኝ በመሆኑ መንግስት ከመቸውም ጊዜ የተለየ ወጣት ተኮር ርብርብ ካላደረገ በስተቀር፣ አገራችን በቅርቡ ለተከሰተው ዓይነት ፖለቲካዊ ችግር በተደጋጋሚ መጋለጧ እንደማይቀር መገንዘብ ይገባል፡፡

መንግስት የወጣቱን ችግር ለማቃለል ባለፉት ዓመታት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እንደተንቀሳቀሰ ይታወቃል፡፡ በተለይ ደግሞ ከ3ኛው አገራዊ ምርጫ በኋላ የወጣቶች የልማትና ተጠቃሚነት ፓኬጅ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት ተቀርፆ በተካሄደው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ብዙ የአገራችን ወጣቶች ተጠቃሚ መሆን እንደጀመሩም ይታመናል፡፡ ይህም ሆኖ ከዚህ ቀደም የተዘጋጀው መፍትሄም ሆነ በዚህ ላይ በመመሰረት የተከናወነው ስራ እጅግ እየሰፋ ከመጣው የወጣት ቁጥርና ፍላጐት ጋር የሚመጣጠን እንዳልሆነ ታይቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለወጣቶች ታስበው የተቀረፁ የልማትና ተጠቃሚነት ፕሮግራሞች በመንግስት በኩል በሚታዩ የተለያዩ ድክመቶች፣ በተለይ ደግሞ በአድልአዊ እና ብልሹ አሰራሮች ምክንያት ሲደነቃቀፉ  የወጣቱ ትውልድ ቅሬታ እንደሚባባስ ታይቷል፡፡ በመሆኑም ባሳለፍነው ዓመት የተከሰቱት ችግሮች በመሰረቱ ከኢኮኖሚ ፍላጐትና ተጠቃሚነት ጋር የተያያዙ በመሆናቸው እነዚህን ችግሮች ራሱን ወጣቱን ትውልድ በቀጥታና ዴሞክራሲያዊ አኳኋን በሚያሳትፍ አቅጣጫ መፍታት ጊዜ የማይሰጥ ተደርጐ ሊወሰድ ይገባዋል፡፡

ባሳለፍነው ዓመት የተከሰተው የፖለቲካ አለመረጋጋት ከተጠቃሚነት አኳያ ያመጣው ችግር የአገራችንን ወጣቶች ብቻ የሚመለከት አልነበረም፡፡ በአገራችን ፈጣን ብቻ ሳይሆን መላውን ህዝብ በየደረጃው ተጠቃሚ የማድረግ ግብ ይዘን በምንገነባው ኢኮኖሚ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ጥቅም በፍትሃዊነት የማስከበር ጉዳይ ሁሌም ቢሆን በተጨባጭ እየተለካና ይህንኑ በፍትሃዊነት እያሳካን በመሄድ ላይ መሆናችን እየተረጋገጠ ሊሄድ የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ቁጥራቸው ሰፊ የሆኑትና በደመወዝ የሚተዳደሩ ወገኖች ከሚያጋጥማቸው የኑሮ ውድነትና የቤተሰብ ኃላፊነት ጋር በተጣጣመ ደረጃ መጠቀም መጀመራቸውን ማረጋገጥ አማራጭ የሌለው ሆኗል፡፡ መንግስት በዚህ ረገድ ያነገበውን የፍትሃዊ ተጠቃሚነት አላማ ለማሳካት በማለም ባለፉት በርካታ ዓመታት ድህነትን ለመቀነስ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መቆየቱና ከጠቅላላ አገራዊ ባጀታችን ውስጥ እጅግ አብዛኛው ድሃ ተኮርና የዜጐችን የማምረት አቅም በመገንባት ላይ ያነጣጠረ እንዲሆን

ማድረጉ ተገቢ ቢሆንም በዚህ ረገድ በተለይ ካስመዘገብነው እድገታችን ጋር በሚመጥን ደረጃ መጠቀም ያልጀመሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ችግር ለማቃለል በተለየ ትኩረት መንቀሳቀስ አንገብጋቢ ሆኖ ይገኛል፡፡

ባሳለፍነው አመት መፍትሄ የሚሹ ሆነው ከታዩት ችግሮች ሌላው በከተሞች አቅራቢያ በሚገኙ ገጠሮች የሚከሰት የአርሶ አደርና የአርብቶ አደር ወገኖቻችን መፈናቀል ጉዳይ ነው፡፡ አገራችን ታዳጊ እንደ መሆኗ ከተሞቻችን በልዩ ልዩ ምክንያቶች ወርድና ቁመታቸው እየጨመረ እንደመጣና ወደፊትም ይህ ሁኔታ እየሰፋ እንደሚሄድ ለመገመት አያስቸግርም፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በገጠር ሰፋፊና ዘመናዊ እርሻዎችን እንዲሁም ትልልቅ የሃይል ማመንጫና የመስኖ ግድቦችን የመስራት ፍላጎታችንም የገጠር መሬትን ከመጠቀም ውጭ ሊሳካ የማይችል ነው፡፡ በመሆኑም ዘመናዊ እርሻዎችና ትልልቅ ግድቦች መስፋፋታቸው ቀጣይ በመሆኑ ይህን ከአርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ መብትና ጥቅም ጋር በተጣጠመ አኳኋን መፈፀም አማራጭ የሌለው ሆኖ ይገኛል፡፡ አርሶ አደሩ የተቻለውን ያህል መሬቱን ከፍተኛ ጥቅም ሊያገኝ በሚችልበት ሁኔታ እንዲያለማው ከማድረግ ጀምሮ ለላቀ አገራዊ ጥቅም በሚፈለግበት ጊዜ ደግሞ ይህንኑ ከአርሶ አደሩና ከአርብቶ አደሩ ዘላቂ፣ ቀጣይና ታዳጊ ተጠቃሚነት ባረጋገጠ መልኩ ልንፈፅመው የሚገባን ሆኖ ይገኛል፡፡ ሃቁ ይህ ቢሆንም በከተሞች አቅራቢያ የሚካሄደውም ሆነ በሌሎች አካባቢዎች የአርሶ አደርና አርብቶ አደር መፈናቀል ከተመጣጣኝ ካሳና የማቋቋም እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ጉድለቶች የሚታዩበት እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህ የተነሳ በተለይ ለከተሞች በቀረቡ አካባቢዎች የሚኖሩ አርሶ አደሮቻችን ለልዩ ልዩ ቅሬታዎች ሲጋለጡ ቆይተዋል፡፡ በመሆኑም በያዝነው አመት ይህን ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል አቅጣጫ ይዘን በመረባረብ የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥና ለማስፋት ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በልማታዊ መንገድ በችሎታና በጥረት ተወዳድረው ለመጠቀም የሚሹ ያሉትን ያህል ካላግባብ የመጠቀም አዝማሚያ የተጠናወታቸው ጥቂት ማህበራዊ ኃይሎች ለአገራዊ እድገት ካበረከቱት አስተዋፅኦ በላይ ሲጠቀሙ የሚታይ በመሆኑ በመነሳት የፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ጉዳይ በጥብቅ መፈተሽና ማስተካከል አስፈላጊ ሆኖ ይገኛል፡፡ እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች አገራችን በከፈተችው እድል ከመጠቀም ወደኋላ የማይሉ ቢሆኑም የመንግስትን ህግ አክብሮ በመንቀሳቀስም ሆነ የግብር ግዴታቸውን በመወጣት ደረጃ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንደማይወጡ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም በኮንትሮባንድና በማጭበርበር እንዲሁም የጉምሩክ ማስተላለፍ ቀዳዳዎችን እና ትስስሮችን በመጠቀም ለአገራዊ እድገት ካበረከቱት አስተዋፅኦ በላይ የሚጠቀሙ ክፍሎች የሚራመዱበትን ህገ ወጥ ተጠቃሚነት በመከላከልና በመቆጣጠር ከዚህም አልፎ የግብር መክፈልና ህግ የማክበር ግዴታቸውን እንዲወጡ በማድረግ የፍትሃዊ ተጠቃሚነት ጉዳይ የማያጠራጥር ተፈፃሚነት እንዲኖረው ማድረግ ይገባል፡፡ ከዚሁ ባልተናነሰ ደረጃ ከከተማ መሬት እና በአንዳንድ ቆላማ አካባቢዎች ከገጠር መሬት ጋር ተያይዞ የሚታዩ ብልሹ አሰራሮችና አላአግባብ የመጠቀም ዝንባሌዎችን ለማስተካከል ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፡፡

በዚህ አጋጣሚ በቅርቡ በአንዳንድ የአገራችን ክልሎች ህገ መንግስታዊ ስርአቱን በኃይል ለመናድ ሲካሄዱ የቆዩ አፍራሽ እንቅስቃሴዎችን መሰረታዊ ባህርይና እንድምታ በትክክል መገንዘብ ተገቢ ሆኖ ይገኛል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በህብረተሳባችን ዘንድ በተለይ ደግሞ በወጣቶቻችን በኩል የተነሱ ፍትሃዊ ጥያቄዎችን ተገን በማድረግ አንዳንድ አፍራሽ ኃይሎች ቅሬታን ወደሁከትና አውዳሚ እንቅስቃሴ ለመቀየር ተረባርበዋል፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ ለዘመናት ከኖረችበት ማሽቆልቆል ወጥታ በእድገት ጎዳና መገስገስ በጀመረችበት በዚህ ታሪካዊ ወቅት በትንሳኤ ላይ መሆናችንን የማይቀበሉ አገሮችና የኒዮ ሊበራል አጀንዳቸውን ሊጭኑብን የተዘጋጁ ኃይሎች፣ ወደትርምስ እንድንገባ አቅደው፣ አገራችንን ለማተራመስ በሰፋት እየተንቀሳቀሱ እንደሆነ ይፋ ሆኗል፡፡ በተለይ ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የማንንም እጅ ሳንጠብቅ በመላ የአገራችን ህዝቦች ተሳትፎና በአገራዊ አቅማችን በመተማመን መገንባት መጀመራችን ያስቆጣቸው አገሮች፣ ረዘም ላሉ ዓመታት ውስጥ ውስጡን ሲዘጋጁ ከርመው በአሁኑ ጊዜ ፅንፈኛ የዳያስፖራ ኃይሎች ከቀሰቀሱት ነውጥ ጋር በመመጋገብ አገራችንን ለማተራመስ በቀጥታ እየተረባረቡ ይገኛሉ፡፡ በቀላሉ ሊያነሳሱዋቸው የሚችሉ ወጣቶችን የጥፋት ሃሳቦች፣ እንዲሁም ክብሪትና ነዳጅ እያስታጠቁ ለአገራችን ቁልፍ ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅኦ ያላቸውን ፋብሪካዎች፣ የአበባ እርሻዎችና ሌሎች ተቋማት በማጋየት ከፍተኛ ውድመት አስከትለዋል፡፡ የግለሰቦችን ቤቶችና ሌሎች ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች አውድመዋል፡፡ ይህን ድርጊት መንግስት ለቴክኖሎጅ ሽግግርና አገራዊ ልማትን ለማፋጠን በማሰብ ያስፋፋውን ዘመናዊ የመገናኛ መሰረተ ልማት ለክፋትና ውድመት በመጠቀም ያስተባበሩት ደግሞ አገራችን በአሸባሪነት የሰየመቻቸው ግለሰቦችና ቡድኖች ናቸው፡፡ የኦነግና ግንቦት ሰባት መሪዎች ከግብፅ መንግስት ተቋማት ጋር እጅና ጓንት በመሆን ባቀናበሩት የጥፋት እንቅስቃሴ በርካታ አገራዊና የውጭ ባለሃብቶችና ሰራተኞቻቸውን ለአደጋ ያጋለጠ የታሰበበት ከፍተኛ ውድመት ፈፅመዋል፡፡ ይህ ከአገራችን ወጣቶች ፍትሃዊ ጥያቄዎች ጋር አንዳችም ተዛምዶ የለውም፡፡

ከፅንፈኛ ዳያስፖራዎች ጀምሮ በአባይ ወንዛችን ላይ የተጠቃሚነት መብታችንን ለማረጋገጥ የጀመርነውን እንቅስቃሴ ለማኮላሸት የሚንቀሳቀሱት እነዚህ ወገኖች፣ በቅርቡ ታላቁን የእሬቻ በዓል ከማወክ ጀምሮ በልዩ ልዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች ያካሄዱት ውድመትና ቃጠሎ በማንኛውም ሚዛን ፍትሃዊነት የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም መንግስት ይህን የመሰለው አፍራሽና ከባድ የውጭ ጣልቃ ገብነትን ታዝሎ የመጣ ፀረ-ኢትዮጵያ እንቅስቃሴ እንዲመከትና ወንጀለኞቹም በጥብቅ በህግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ በቃጠሎ የወደሙ ንብረቶች በተለይ ደግሞ የምርት ተቋማት አገራችንና

ህዝቦቿ ከውጭ የልማት አጋሮቻችን ጋር በመተባበር በአፋጣኝ መልሰው እንዲገነቡና ለላቀ ምርታማነት እንዲበቁ ጠንካራ ርብርብ ይደረጋል፡፡ በመሆኑም መላ የአገራችን ህዝቦች ኢትዮጵያን እንደፈራረሱት የሰሜን አፍሪካና የመካከለኛው ምስራቅ አገሮች ለማተራመስ የሚደረገውን ይህን አፍራሽና አሳፋሪ ሙከራ መንግስትና ህዝብ በጀመሩት መንገድ በጋራ ይፋለሙታል፡፡

**የተከበራችሁ የህዝብ ተወካዮች እና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች አባላት፣**

**የተከበራችሁ መላ የአገራችን ህዝቦች፣**

2ኛውን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተግባራዊ ማድረግ በጀመርንበት ዓመት የተከሰቱት ችግሮች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንድምታ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታችንን በማዳበር ልንፈታቸው የሚገባ ልዩ ልዩ ፖለቲካዊ ጉዳዮችም እንዳሉም አመላክተውናል፡፡ በዚህ ረገድ ቀዳሚው ጉዳይ በአገራችን የብሔር ብሔረሰቦችን መብት መሰረት አድርገው የሚነሱ የማንነት ጥያቄዎችን በህገ-መንግስታችን በጥብቅ በመመራት መፍታት እንዳለብን ሊሰመርበት የሚገባ መሆኑ ነው፡፡ ለማንም ግልፅ እንደሚሆነው ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓታችን የተዋቀረው ኢትዮጵያ የብዙ ህዝቦች አገር የመሆኗን እውነታ ያለማቅማማት በመቀበል ነው፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ የአንድ ቋንቋ፣ ወይም ባህል አገር ሳትሆን የብዙ ቋንቋዎች፣ ሌሎች የማንነት መገለጫዎች ባለቤት የሆኑ ብዙ ህዝቦች እናት የሆነች አገር ነች፡፡ ቀደም ሲል በአገራችን ይህን እውነታ በመካድ ብሔር ብሔረሰቦቻችን ካላግባብ የተያዙበት መንገድ ለግጭትና የእርስ በርእስ ለዘመናት ጦርነት መንስዔ እንደነበር በመገንዘብ አዲሱ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ብዝሃነትን በማወቅና በመቀበል እንዲሁም በአግባቡ በማስተዳደር ላይ እንዲመሰረት ተደርጓል፡፡ ይህም በመሆኑ አገራችን ለ25 ዓመታት የዘለቀ አስተማማኝ ሰላም ተጎናፅፋ ቆይታለች፡፡

ላለፉት 25 ዓመታት የተገነባው ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ከሞላ ጎደል የሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄ በተግባር የመለሰ ቢሆንም፣በተወሰነ ደረጃ መሰረተ ሃሳቡ ተግባራዊ ያልተደረገባቸው ማህበረሰቦች ደግሞ እንደነበሩ ታይቷል፡፡ በዚህ የተነሳ ዘግይተው ጥያቄ የሚያቀርቡ ራሳቸውን የቻሉ ማህበረሰቦች የተከሰቱ ሲሆን፣ የነዚህ ህዝቦች ጥያቄ በዴሞክራሲያዊው ህገ መንግስታችን ማዕቀፍ ሊስተናገድ የሚችልና የሚገባው ሆኖ ይገኛል፡፡ ይሁንና ይህን የመሰለው ፍትሃዊ ጥያቄ በወቅቱ ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኝ ባለመደረጉ በአንዳንድ አካባቢዎች ለግጭት መንስኤ መሆን ጀምሯል፡፡ ይህም ሆኖ ግጭቱ የተቀሰቀሰው አንዳንድ ወገኖች እንደሚያስቡት ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአታችን ለግጭት መንስዔ ስለሆነ፣ ወይም ደግሞ በማንነት ዙሪያ የሚነሱ አዳዲስ ጥያቄዎችን በብቃት ለማስተናገድ የሚቸገር በመሆኑ አይደለም፡፡ ፌዴራላዊ ስርአታችን በመሰረታዊ ባህሪው የማህበረሰቦችን ማንነት ማክበር በመሆኑ ችግር ፈች እንጅ ችግር ፈጣሪ ወይም አባባሽ አይደለም፡፡ ይህ ሩቅ ሳንሄድ አዲሱ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአት፣ አገራችን በዘመናዊ ታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ሩብ ምዕተ ዓመት የሞላው ረዥም የሰላም ዘመን እንድትኖር፣ ህዝቦቿ ለሃያ አምስት ዓመታት በሰላም፣ በፍቅርና በመካባበር እንዲኖሩ ያስቻለን በመሆኑ የሚረጋገጥ ነው፡፡ ስለሆነም ችግሩ በተጨባጭ የተነሳው ከስርአቱ ባህሪ ሳይሆን፣ ማህበረሰቦች የሚያነሱትን የማንነት ይከበርልን ጥያቄ ከህገ-መንግስታዊው ድንጋጌ በመነሳትና ይህንኑ በጥብቅ በማክበር መመለስ ሲገባ ከዚሁ ተቃራኒ በሆነ አያያዝ በአንዳንድ አካባቢዎች በመፈፀሙ ነው፡፡

ከዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ አኳያ ሌላው ትኩረት የሚሻ ሆኖ የተገኘው ራሱን ዴሞክራሲያችንን ከእድገታችን ጋር በተገናዘበ ሁኔታ ተግባራዊ የማድረግ ጉዳይ ነው፡፡ አገራችን ባፀደቀችውና በምትመራበት ህገ-መንግስት ዴሞክራሲያዊ የአስተዳደር ስርዓትን መርጣለች፡፡ የመረጥነው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለአንዴና ለሁልጊዜ ረግቶ የሚቀመጥ ሳይሆን ከአገሪቱ የእድገት ደረጃ ጋር ተገናዝቦ ሁሌም ቢሆን በታዳጊነት መገንባትና እየዳበረ መጓዝ ያለበት ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት በአገራችን ብዝሃነት ያሉዋቸው ማህበረሰቦች እንደሚገኙና እነዚህም የየራሳቸው ልዩ ልዩ ፍላጎቶች ያሏቸው መሆኑን በመገንዘብ የተለያዩ ጥቅሞችን በማቻቻልና በማጣጣም ልትመራ የሚገባት እንደሆነ ታምኖበት በዚሁ ቅኝት ስትራመድ ቆይታለች፡፡ ከሁሉ በፊት በጥቅሞች መካከል የሚከሰቱ ልዩነቶች ሁሉ በዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ መንገድ እንዲገለፁ ማድረግ፣ አገራችን በተረጋጋ መንገድ ለመቀጠል እንድትችል የሚያደርጋት ቁልፍ እንደሆነ ታምኖበት ፍላጎቶች በነፃነት እንዲገለፁ ሲደረግም ቆይቷል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከመልካም አስተዳደር ችግርና ከመሳሰሉት ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩ ቅሬታዎችን በዴሞክራሲያዊ መንገድ ከማስተናገድ አኳያ በመንግስትም ሆነ በህብረተሰብ ደረጃ ክፍተቶች እንዳሉ ተስተውሏል፡፡ በመንግስት በኩል ለህዝብ ቅሬታ መከሰት ምክንያት የሆኑ ችግሮችን በፍጥነት ካለማረም ጀምሮ ህዝብ የተሰማውን ቅሬታ በዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ መልክ ይገልፅ ዘንድ በበቂ ሁኔታ ያለማስተናገድ ችግር ታይቷል፡፡ በአንዳንድ የህብረተሰባችን ክፍሎች በኩል ደግሞ ህገ-መንግስታዊ ስርዓታችን ማንኛውንም ጥያቄ ሆነ የህዝብን ፍላጎት በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ለማራመድ የሚያስችል ብቁ የመታገያ ማዕቀፍ እንዳጎናፀፈን በውል ባለመገንዘብ በጥቂቱም ቢሆን ከህገ መንግስታዊ ስርአቱ ውጭ በሚታዩ ሁከቶች በመሳተፍ መልክ የሚታዩ ስህተቶች ተስተውለዋል፡፡ አልፎ አልፎ በተለይ ደግሞ በወጣቶቻችን ዘንድ ህግ በመጣስ መንግስትና ህዝብን ለማጋጨት የሚሹ አፍራሽ ፀረ- ሰላም ሃይሎችን በየዋህነት በመከተል የተሳሳቱ የትግል ስልቶች የመጠቀም አዝማሚያ ታይቷል፡፡ በዚህ ረገድ ፍላጎትን በሰላማዊ ሰልፍ አማካይነት

ከመግለፅ መብት ጋር ተያይዘው የተከሰቱ ችግሮችን ማስታወስ ይቻላል፡፡ እነዚህ ችግሮች በመንግስትም ሆነ በህብረተሰብ ደረጃ ዴሞክራሲያችንን በማበልፀግ ተጨማሪ እርምጃዎች መራመድ እንዳለብን የሚያመላክቱ ሆነዋል፡፡

ዴሞክራሲያዊ ስርዓታችንን ከማበልፀግ አኳያ ሌላው ትኩረት የሚሻው ጉዳይ በአገራችን የፍላጐት ብዝሀነት እንዳለ ተገንዝቦ እነዚህን በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለመግለፅ የሚቻልበት ሁኔታ እንዲፈጠር ከማድረግ አኳያ የምክር ቤቶቻችንን ተዋፅኦ የማጐልበት ጉዳይ ነው፡፡ እንደሚታወቀው  አገራችን በምትከተለው የአብላጫ ድምፅ የምርጫ ስርዓት በመመራት ባለፉት ሀያ አምስት ዓመታት በድምሩ  ለአስር ጊዜ አገራዊ፣ ክልላዊና ከባቢያዊ ምርጫዎች ተካሂደዋል፡፡ በእነዚህ ምርጫዎች የብዙ ፓርቲዎች ተሳትፎ የነበረ ሲሆን፣ በተለይ ባለፉት ሁለት ምርጫዎች እንደተከሰተው በምክር ቤቶቻችን የገዥው ፓርቲ ሙሉ የበላይነት ያለበት ሁኔታ ተስተውሏል፡፡ ይህ በዴሞክራሲያዊ መንገድ በተካሄደ ምርጫ  የህዝብ ድምፅ ያስገኘው ውጤት እንደሆነ ባያጠያይቅም፣ ተቃዋሚዎችን የመረጡ የህብረተሰብ ድምፆች በመኖራቸውና በአብላጫ ድምፅ ወንበር  የማግኘት የምርጫ ሥርዓታችን መሠረት በአገራችን ወሳኙ የስልጣን አካል በሆነው ምክር ቤት የማይወከሉ ድምፆች እንዲኖሩ አድርጓል፡፡ በመሆኑም ከገዥው ፓርቲ በተለዩ ፓርቲዎች የሚወከል ጥቅምና ፍላጐት ያላቸው ማህበረሰቦችን የሚወክሉ ፓርቲዎች በምክር ቤቶቻችን ውስጥ የመሳተፍ እድል ሳያገኙ ቀርተዋል፡፡ ስለሆነም ይህን የመሰለው ሁኔታ ስርዓታችን ተረጋግቶ እንዲቀጥል ከማድረግ አኳያ የራሱ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያስከትል በመሆኑ፣ በተቻለ መጠን ከቀጣዩ ምርጫ በፊት ዴሞክራሲያዊ መድረኮችን በማስፋትና በቀጣዩ ምርጫም በህግ ማእቀፍ በተደገፈ አኳኋን የህዝብ ምክር ቤቶች የተለያዩ ድምፆች የሚሰማባቸውና የሚፎካከሩባቸው መድረኮች  እንዲሆኑ በማድረግ ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታችን ለፓርቲዎች ተሳትፎ ከሚሰጠው ትኩረት ባልተናነሰ ደረጃ፣ በከፍተኛ ትምህርትና በልዩ ልዩ የስራ ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ምሁራንን ጨምሮ በተለያዩ የሲቪክ ማህበረሰብ አደረጃጀቶች ውስጥ የሚታቀፉ ዜጎችን በቀጥታ በማሳተፍ ጠቃሚ ሃሳቦቻቸውን ሁሉ ለአገር ግንባታ ማዋል ይጠይቃል፡፡ በዚህ ረገድ ልዩ ልዩ መድረኮችን በመክፈት የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ለማረጋገጥ የተለያዩ ጅምር ጥረቶች እንዳሉ ባያጠያይቅም እስካሁን የተደረጉት ጥረቶች በቂ እንዳልሆኑ ለመገንዘብ አያስቸግርም፡፡ በተከፈቱት መድረኮች የሚቀርቡ አስተያየቶችን በውል አዳምጦ ጠቃሚዎቹን ያለማቅማማት በመውሰድ፣ የተሳሳቱና ጐጅ አስተያየቶችን ደግሞ በአመክንዮና ጭብጦች ታግዞ በማስተካከል፣ የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎና አስተዋፅኦ ወደሚገባው ደረጃ ማድረስ አስፈላጊ ሆኖ የሚገኘው ከዚህ የተነሳ ነው፡፡

በአገራችን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታን በታዳጊ አኳኋን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ትኩረት የሚሻ እንደሆነ የተረጋገጠው ሌላው ጉዳይ በስነ ምግባርና ስነ ዜጋ እሴቶች የታነፀ ትውልድ የመፍጠር ጉዳይ ነው፡፡ በየትኛውም ዓለም ዜጐች መብትና ግዴታቸውን በውል ተገንዝበው፣ ከእያንዳንዳቸው የሚጠበቀውን ኃላፊነት እየተወጡ፣ በመብቶቻቸው ላይ ደግሞ የማይደራደሩ ሆነው እስከተገኑ ድረስ አገሮች በእድገት ጐዳና እንደሚራመዱ ይታወቃል፡፡ የላቀ የዜግነት እንቅስቃሴም መልካም አስተዳደርን ለማስፈንም ጭምር ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በእኛም አገር ከዚህ የተለየ ሊሆን አይችልም፡፡ ዜጐች በአገር ግንባታ ሂደት ንቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ትምህርትና ክህሎትን ማስፋፋት አማራጭ የሌለው ቢሆንም፣ ከዚሁ በማይነጠል መልኩ በስነ ምግባርና ስነ ዜጋ እሴቶች የታነፀ ትውልድ የመፍጠር ጉዳይ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ ይገኛል፡፡

**የተከበራችሁ የህዝብ ተወካዮች እና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች አባላት፣**

**የተከበራችሁ መላ የአገራችን ህዝቦች፣**

ከወቅታዊ የአገራችን ሁኔታ በመነሳት እነዚህን የመሳሰሉ ጉዳዮች አጣዳፊ መፍትሔ የሚሹ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ዛሬም እንደ ትላንቱ አገራችንን በታለመው ፈጣን የእድገት አቅጣጫ ለማስቀጠልና የህዝብ ተጠቃሚነትን ለማጐልበት ሁለተኛውን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ይበልጥ ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ የማድረግ ጉዳይ ልዩ ትኩረት የሚሻ ሆኖ ይገኛል፡፡ በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዳችን የተሳካ አፈፃፀም በመበረታታት የነደፍነው ሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ወደ ተግባር ከተሸጋገረ አንድ ዓመት አስቆጥሯል፡፡ በዚህ መሰረት ባሳለፍነው ዓመት በሁሉም መስኮች እቅዳችንን ተግባራዊ ለማድረግ የተንቀሳቀስን ቢሆንም አፈፃፀማችን በልዩ ልዩ ተግዳሮቶች ተፅዕኖ ስር ለማለፍ የተገደደ እንደነበር ከመላ የአገራችን ህዝቦች የተሰወረ አይደለም፡፡ ድርቁና ከሞላ ጐደል አብዛኛውን የዓመቱን ክፍል የሸፈኑ የሰላምና መረጋጋት ችግሮች በአፈፃፀማችን ላይ ራሳቸውን የቻሉ ተፅእኖዎች ያሳደሩ ነበሩ፡፡ ምንም እንኳ በትልልቆቹ ፕሮጀክቶቻችን አፈፃፀምና የተሻለ ዝናብ ከመገኘቱ ጋር ተያይዞ በታየው የተሻለ የግብርና ምርታማነት እና በኢንዱስትሪ መስክ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች በመከናወናቸው ኢኮኖሚያችን አሁንም በፈጣን እድገት ጐዳና መቀጠሉ የተረጋገጠ ቢሆንም፣ አገራችን ከፈጠረችው መልካም መነሻና ካላት ድልብ አቅም በመነሳት ለላቀ ውጤት ተግተን መስራት የሚገባን ወቅት ላይ እንገኛለን፡፡ ባሳለፍነው ዓመት ያጋጠሙ ችግሮች በአፈፃፀማችን ላይ ያሳደሩትን  ተፅዕኖ በመቋቋም ሳንወሰን በዚህ ምክንያት የተፈጠረውን ክፍተት በሚያካክስ ደረጃ ለውጥ ለማምጣት መረባረብ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ በመነሳት በያዝነው ዓመት የግብርና ፕሮግራማችን በተለምዶ ጥሩ እድገት ሲያሳዩ የቆዩትን የግብርና መስኮች ለላቀ ውጤታማነት ለማብቃት እንቀሳቀሳለን፡፡ ከግብርና ዘርፉ ውስጥ በቀላሉ ከፍተኛ መሻሻል ልናሳይ የምንችለው አሁንም በተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤና በዚሁ ተደግፎ የመስኖ ስራችንን በማስፋፋት በሰብል ምርት እድገት በማምጣት በመሆኑ እነዚህን በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ አልመን መንቀሳቀስ ይኖርብናል፡፡ የተፈጥሮ ሃብት ልማት አገራችን ያላትን እምቅ የግብርና አቅም አሟጠን እንድንጠቀምበት የሚያስችለን ዋናው መግቢያ በመሆኑ አካባቢውን ተግቶ የመለወጥ ባህል ማዳበር በጀመረው አርሶ አደርና አርብቶ አደሮቻችን እንዲሁም በየገጠሩ ወጥተው ወርደው ህዝብን በሚያስተምሩ ሙያተኞቻችን በመተማመን የመሬታችንን ለምነትና የውሃ ሃብታችንን ለማበልፀግ መረባረብ ልዩ ትኩረት እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡ በምንገኝበት የእድገት ደረጃ የሰብል ምርት የህልውናችን መሰረት በመሆኑና በዚህ መስክ የምናስመዘግበው እድገት ሁሉ በገጠርም ሆነ በከተማ የህዝባችንን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ቁልፍ ተፈላጊነት ያለው እንደሆነ በመገንዘብ ይህን ለማልማት መላ አቅማችንን እናረባርባለን፡፡

እነዚህ እንደተጠበቁ ሆነው የአገራችንን አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ከፍተኛ ዋጋ ወደሚያስገኙ ምርቶች ለማሸጋገር ተፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ የማሟላት ጉዳይ በእቅዱ መሰረት ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ ከፍተኛ ዋጋ ከሚያስገኙ የግብርና ምርቶች መካከል በአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ የሚለሙ እንደቡና የቅባት እህሎች፣ አትክልትና ፍራፍሬዎች፣ ደኖችና የእንስሳት ሃብታችን ልማት ዋናዎቹ ሲሆኑ በዚህ ረገድ የአገራችን ያላትን ድልብ አቅም በአፋጣኝና በብቁ ዝግጅት ወደማልማት እንሸጋገራለን፡፡ ከዚህ በመነሳት የግብርና ልማታችን በአንድ በኩል በቀላሉ ከፍተኛ የእሴት ጭማሪ ልናመጣባቸው በሚገባን መስኮች መረባረብን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የቀጣዩ የግብርና ዘርፍ እድገት አምጭ መስኮችን ለይቶ በበቂ ቅድመ ዝግጅት ወደማልማት መሸጋገርን በታሳቢነት የሚወስድ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በገጠር ከግብርና ልማታችን ጋር በማያያዝ ሊመጣ ከሚገባው እድገት ዋናው ተጠቃሚ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ መሆናቸውን ከማረጋገጥ በተጨማሪ የእነዚህ ወገኖች የመሬት ተጠቃሚነት ዋስትና ይበልጥ አስተማማኝ እንዲሆን ከማድረግ ጀምሮ ለምርታቸው ተገቢውን ዋጋ አግኝተው ተጠቃሚነታቸው እንዲሰፋ የማድረግ ጉዳይ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ በተለይ ደግሞ አይቀሬ ከሆነው የከተሞች መስፋፋት ጋር ተያይዞ የገጠር መሬትን ለላቀ ጥቅም ለማዋል የሚደረግ እንቅስቃሴ የአርሶ አደሩንና የአርብቶ አደሩን መሰረታዊና ታዳጊ ጥቅሞች አሳልፎ በማይሰጥ መንገድ እንደሚፈፀም ይረጋገጣል፡፡ በዚህ ረገድ ክፍተት ያለባቸውን ነባር ህጎችን የማስተካከል፣ በአፈፃፀም የሚታዩ ስህተቶችን ታግሎ የማረም፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም አዳዲስ የህግ ማዕቀፎችን የማዘጋጀትና ከሁሉ በላይ ደግሞ ከመሬታቸው ለልማት ሲባል የሚነሱ አርሶ አደሮችንና አርብቶ አደሮችን በሚያሳትፍ አኳኋን እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡

አገራችንን በግብርናው ዘርፍ ለማሳደግ የሚካሄደው ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ ሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ወደ ኢንዱስትሪ መር ልማት ለመሸጋገር ዝግጅት የምናደርግበት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በዚህ መሰረት ከወዲሁ ኢንዱስትሪን ለማስፋፋት የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች ተቀርፀው ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዱ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ሲሆን፣ በዚህ ረገድ በዋና ዋና ማዕከላት ላይ የሚገነቡ ትልልቅ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ግንባታ በመካሄድ ላይ ነው፡፡ በሌላ በኩል የግብርና ምርቶቻችንን ባለቀለት መልኩ ለማዘጋጀት የሚያግዙ ኢንዱስትሪያዊ ተቋማት የሚስፋፉባቸው በርካታ የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት በመካሄድ ላይ ነው፡፡ እነዚህን ፓርኮች በአግባቡና በትክክል በመምራትና በማስተዳደር በተለይ ደግሞ የአገራችን ባለሀብቶች አቅም መገንቢያ ሆነው እንዲያገለግሉ በማድረግ ጭምር እሴት ከመፍጠር ፋይዳቸው ባሻገር የግሎባላይዜሽንን ማእከል ለማቋቋም የሚያስችሉን መወዳደሪያ አቅሞች የምንፈጥርባቸው እንደሚሆኑ ይታመናል፡፡

ከዚህ በመነሳት በኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ፖሊሲያችን መሠረት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት በተጠናከረ አኳኋን የሚከናወን ይሆናል፡፡ አገራዊ ባለሃብቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮቻችን ውስጥ በበቂው እንዲሳተፉ ከማድረግ በማይተናነስ አኳኋን፣ በእነዚህ መስኮች የሚሰማሩ የውጭ ባለሃብቶችም ለአገራዊ ልማት ስትራትጂያችን ተፈፃሚነት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የሚያበረክቱበትን ሁኔታ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተለይ ደግሞ ፓርኮቹ እጅግ የምንጓጓለትን የቴክኖሎጅ ሽግግር ለማስፈፀም ቁልፍ አስቻይ መድረኮች መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባናል፡፡

**የተከበራችሁ የህዝብ ተወካዮች እና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች አባላት፣**

**የተከበራችሁ መላ የአገራችን ህዝቦች፣**

ባሳለፍነው ዓመት ከተከሰተው የወጣቶች ጥያቄ ጋር በማያያዝ አስፈላጊነቱ እጅግ ጎልቶ የመጣው የልማት አውድማ በገጠር የኢንዱስትሪ ልማትን የማስፋፋት ጉዳይ ነው፡፡ ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ልማትን ለማስፋፋት የትላልቅ ፓርኮች መስፋፋት ጠቃሚና አስፈላጊ ቢሆንም፣ በገጠር የሚገኘውን ሰፊ የወጣት ሃይል አቅም ለመጠቀምም ሆነ በቀላሉ ኢንዱስትሪያዊ ግብዓት አድርገን ልንጠቀምበት የምንችለውን ሰፊ የተፈጥሮ ሃብት ከማልማት አኳያ የገጠር አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪን የሚያክል የለም፡፡ የገጠር አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪ በኮንስትራክሽንና በአግሮ ፕሮሰሲንግ መስኮች ከፍተኛ እሴት የመጨመር ፋይዳ ያለው እንደሆነ በፍጥነት እያደጉ ካሉ አገሮች ታሪክ በመነሳት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በተለይ ደግሞ የገጠር አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪን የአገራችን ወጣቶች በሰፊው የስራና የሃብት ፈጠራ

እድልነት እንዲጠቀሙበት ለማድረግ በርግጥም ዘርፉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ትርጉም ያለው እድገትና የህዝብ ተጠቃሚነት ልናረጋግጥ የምንችልበት ነው፡፡ በመሆኑም በአገራችን ኢንዱስትሪያዊ ልማትን በማፋጠን ልናመጣው የምንፈልገውን ሽግግር አስተማማኝ ለማድረግ እንችል ዘንድ ለገጠር የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ልማት የተለየ ትኩረት እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡ ይህንን ለማድረግም ክልሎች መለስተኛ ከተሞችንና የገጠር ማዕከላትን መሠረት አድርገው ሰፊ እንቅስቃሴ በተቀናጀ ሁኔታ እንዲያከናውኑ ይጠበቃል፡፡ የፌዴራል መንግሥትም ሁለንተናዊ የማስፋፀሚያ ድጋፎችን በማድረግ የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት በቅንጅት መሥራት ይጠበቅበታል፡፡

ሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዳችን በመሰረተ ልማት አውታሮች ግንባታ ልዩ ትኩረት መስጠቱ ይታወሳል፡፡ ይህን መነሻ በማድረግ አገልግሎቱን ለማስፋፋት ከሜጋ ኘሮጀክቶች ጀምሮ ከባቢያዊ ፋይዳ እስካላቸው አነስተኛ ልዩ ልዩ የመሰረተ ልማት ኘሮጀክቶች ታቅደው ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አገራችን የእድገት ደረጃ ላይ ከሚገኝ ከየትኛውም ለተመሳሳይ አገር በላቀ ደረጃ የመሰረተ ልማት ግንባታ በማከናወን ላይ ትገኛለች፡፡ በአገራችን በመካሄድ ላይ ያለው የመሰረተ ልማት ግንባታ በተለይ ትልልቆቹ ኘሮጀክቶች ከፍተኛ የገንዘብ ወጭ የሚጠይቁና እስኪጠናቀቁ ድረስም ረዥም ጊዜ የሚወስዱ ናቸው፡፡ በዚህ ዙሪያ መንግስት ለእድገታችን አማራጭ የሌላቸውን እንደታላቁ የህዳሴ ግድብና የባቡር ልማት እንዲሁም የመሳሰሉ ኘሮጀክቶች በላቀ ቁርጠኝነት የሚቀጥልባቸው ይሆናል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ያለንን ውሱን አገራዊ ፋይናንስ በሰፊ ኢንዱስትሪያዊና የዘመናዊ ግብርና ሴክተር ላይ የተሰማራ አገራዊ ባለሃብት በተለይ ደግሞ ወጣት ባለሃብት ለመፍጠር በሚያስችለን አቅጣጫ ማሰማራት ይገባናል፡፡ እንዲሁም በመሰረተ ልማት ስራዎቻችንና እሴት የመጨመር ቀጥተኛ ፋይዳ ባላቸው ሴክተሮች መካከል የሚኖረውን የኢንቨስትመንት ፋይናንስ ስምሪት ሚዛን እያስተካከሉ መሄድ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ ከዚህ በማይተናነስ መልኩ በመንግስት ኘሮጀክቶች አፈፃፀም ላይ የሚታየውን መጓተትና ብክነት ለመቆጣጠር ከመቸውም ጊዜ የተለየ ትኩረት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ስራ ተቋራጮች ጥራት ያለው ስራ ማከናወናቸውን ከማረጋገጥ ጀምሮ በኮንትራት አስተዳደር ዙሪያ ከውስጥም ከውጭም የሚታዩ ብልሽቶችን በህግ ተጠያቂነት ጭምር በማስተካከል በኘሮጀክቶች ዙሪያ የሚታየውን ጉድለት ለመቆጣጠር እና ለማስተካከል ትኩረት ይሰጣል፡፡

**የተከበራችሁ የህዝብ ተወካዮች እና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች አባላት፣**

**የተከበራችሁ መላ የአገራችን ህዝቦች፣**

ከፍ ሲል ከተዘረዘሩት የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ማሳያ ጉዳዮች በመነሳት በያዝነው ዓመት ለየት ያለ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ስራዎችን በአጭሩ ማመላከት ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ ከሁሉ በፊት ትኩረት የሚሰጠው የወጣቶችን ችግር ለመቅረፍ ይሆናል፡፡ የአገራችን ወጣቶች የወደፊቷ ኢትዮጵያ ገንቢዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ ዛሬ በምንገኝበት ወቅት የራሳቸው ፍትሃዊ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም የፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ፍላጐትና ጥያቄዎች ያሏቸው በመሆኑ እነዚህን በአግባቡ የመመለስ ጉዳይ ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ ከወጣቶች ጥያቄዎች መካከል ሁሉንም ችግሮቻቸውን አስተሳስሮ የመፍታት እድል የሚሰጠው ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን የማረጋገጥ ጉዳይ በመሆኑ ከያዝነው ዓመት ጀምሮ ወጣቶች የስራና የሃብት ፈጠራ እድላቸው በተጨባጭ እውን እንዲሆንና እየሰፋም እንዲሄድ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፡፡ ይህ ጥረት ይሳካ ዘንድ የፋይናንስ አቅርቦትን ማስፋት፣ አዳዲስ የኘሮጀክት ሃሳቦችን ማመንጨትና አሳታፊ የአፈፃፀም ስርዓት መገንባትን የግድ ይላል፡፡

በዚህ መሰረት መንግስት በያዝነው ዓመት በሁሉም አካባቢዎች የሚገኙ ወጣቶችን ለኢኮኖሚያዊ ልማት ተጠቃሚነት የማብቃት ዓላማ ያለውና ለዚህ ዓላማ ብቻ የሚውል የወጣቶች ተንቀሳቃሽ ፈንድ በማቋቋም ስራውን ይጀምራል፡፡ ለዚህም ሲባል ለፈንዱ ማቋቋሚያ የአሥር ቢሊዮን ብር ተመድቧል፡፡ የፈንዱን አስተዳደርና አጠቃቀም በተመለከተ በሚወጣው የህግ ማዕቀፍ መሠረት የወጣቶችን ተሳትፎና ቁጥጥር በሚያረጋግጥ ተዘዋዋሪ አኳኋን ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ ለወጣቶች የስራ መነሻ ይሆን ዘንድ ከተመደበው ፈንድ ጐን ለጐን የስራ ፈጠራው የሚያተኩርባቸው መስኮች የተለዩ በመሆኑ ከወጣቶች ጋር ተመክሮባቸው መግባባት ላይ እንዲደረስባቸው ይደረጋል፡፡ መንግስት የወጣቶች ፈንድ አጠቃቀምና የኘሮጀክቶች ትግበራ መሰረተ ሃሳቦችን ከሚመለከታቸው የአመራር አካላትና ከወጣቶች ጋር በመመካከርና ተፈላጊውን የአቅም ግንባታ ድጋፍ በመስጠት የሚያስፈፅም ሲሆን፣ የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተቀየሰው ኘሮግራም በየጊዜው እየተገመገመ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ የሚወሰድበት እንዲሆን ይደረጋል፡፡

የፐብሊክ ሰርቪሱን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ከዚህ ቀደም ለሀገራችን መምህራን እና የፍትህ አካላት ዳኞችን ጨምሮ አቅም የፈቀደውን ያህል ማሻሻያ ለማድረግ ጥረት መደረጉ ይታወቃል፡፡ የአገራችን ፐብሊክ ሰርቪስ ከእድገታችን ጋር ተመጋጋቢ በሆነ ደረጃ ተጠቃሚ እየሆነ እንዲሄድ ለማድረግ በየወቅቱ የዋጋ ግሽበትን ታሳቢ ያደረገ የደመወዝ ማስተካከያ እየተደረገ መምጣቱም ግልጽ ነው፡፡ በዘንድሮ ዓመትም የሥራ ደረጃ ማስተካከያና ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ መርህን የተከተለ የሪፎርም ሥራ ጥናትና የሙከራ ትግበራ እስከ ዓመቱ አጋማሽ በማጠናቀቅ አቅም የፈቀደውን ማስተካከያ

ለማድረግ ጥረት ይደረጋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የመከላከያና የፖሊስ ሠራዊት አካላትን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የተጀመሩ ስራዎችን አጠናክሮ ከማስቀጠል ጐን ለጐን የኑሮ ውድነትን ታሳቢ ያደረገ የደሞዝ ማስተካከያ የሚደረግ ይሆናል፡፡

ከፍ ሲል ከተገለፁት የህዝብን ተጠቃሚነት በተለይ ደግሞ በልዩ ሁኔታ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች መብትና ጥቅም ከማስከበር በተጨማሪ የአገራችንን ዴሞክራሲ ለማጐልበት የተለየ እንቅስቃሴ ይደረጋል፡፡ ከዚህ አኳያ ቀዳሚው ስራ በገዥው ፓርቲና በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል በሚደረግ ድርድር የምርጫ ህጋችንን የማሻሻል ጉዳይ አንዱ ይሆናል፡፡ አገራችን የምትመራበት የምርጫ ህግ በብዙ አገሮች እንዳለ የሚሰራበት ቢሆንም፣ ከእኛ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት የሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ድምፅ ሊሰማ የሚችልበትን አስተማማኝ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ ከመገኘቱ ጋር የህግ ማሻሻያ ይደረጋል፡፡ ስለሆነም የምርጫ ህጋችን የአብላጫ ድምፅና የተመጣጣኝ ውክልና ስርዓቶችን በትክክለኛ ሚዛን ያጣመረና የሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ድምፅ የሚሰማባቸው ምክር ቤቶች እንዲኖሩን ለማድረግ በሚያስችል ሁኔታ እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡ ይህም በፓርቲዎች መካከል በሚካሄድ የሰጥቶ መቀበል መርህ የሚገዛና አገራዊ ጥቅማችንን ማዕከል ባደረገ ግልፅነትን የተላበሰ የድርድር ሂደት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

ከዚህ ጎን ለጎን ዴሞክራሲያችንን ከማስፋት አኳያ በሁሉም ደረጃዎች የሚገኙ ባለድርሻ አካላት ትርጉም ያለውና ውጤታማ ተሳትፎ የሚያደርጉበት ስርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡ በዚህ ረገድ ከከፍተኛ ጀምሮ እስከዝቅተኛው እርከን ድረስ የሚገኙ የመንግስት ኃላፊዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚኖራቸው ተሳትፏዊ መስተጋብር ህግና ስርዓት እንዲበጅለትና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ አግባብ እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡ መንግስት በዚህ ረገድ ያለው አፈፃፀም በቀጣይነት ለባለድርሻ አካላት እየቀረበ የሚገመገምበትና ተፈላጊ የማስተካከያ እርምጃዎች የሚወሰዱበት ስርዓት በስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

ህገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓታችን በሚደነግገው መሰረት ከማንነት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ተገቢ ጥያቄዎች በዚህ በጀት ዓመት ውስጥ የተሟላ እልባት እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም የአስፈፃሚውን አካል ሥራዎች ውጤታማ ለማድረግ የሚያከናውናቸውን የቁጥጥር ሥራ መልካም ጅምሮች የበለጠ ከማጐልበት በተጨማሪ የተያያዝነውን የዕድገትና ትራንፎርሜሽን ጉዞ ለማሳካት የሚያግዙ አዋጆችን እንደሚያወጣ ይጠበቃል፡፡ ከዚህ አኳያ በዘንድሮ ዓመት የኦሮሚያ ክልል በአዲስ አበባ ላይ ያለውን ልዩ ጥቅም ለመደንገግ የሚወጣውን አዋጅ ጨምሮ ሌሎች በርካታ አዋጆች የሚወጡ ይሆናል፡፡

**የተከበራችሁ የህዝብ ተወካዮች እና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች አባላት፣**

**የተከበራችሁ መላ የአገራችን ህዝቦች፣**

መንግስት በነደፈው መሰረታዊ የለውጥ አቅጣጫ እየተመራ ላለፈው ሩብ ምእተ ዓመት አገራችንን ከማሽቆልቆል ጉዞ አውጥቶ በእድገት ጐዳና እንዳረማመዳት ከመላ ህዝባችን የተሰወረ አይደለም፡፡ በተለይ ደግሞ ባለፉት አሰራ አምስት ዓመታት በዓለም ፈጣን የሚባለውን እድገት በማስመዝገብ ስንጓዝ መቆየታችን አያከራክርም፡፡ ከዚህ መሰረታዊ ስኬት በመነሳት መላ የአገራችን ህዝብች በሁሉም መስክ የተጀማመሩ መልካም ስራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ልባዊ ፍላጐት እንዳላቸው መንግስት በጥብቅ ይገነዘባል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አገራችንን ወደ ፊት ባራመድንባቸው በእነዚህ ዓመታት፣ ቀስ በቀስ እያደጉ የመጡ በርካታ ችግሮች እንዳጋጠሙን ይታወቃል፡፡ እነዚህ ችግሮች በአንድ በኩል ከፍ ሲል እንደተገለፀው ከእድገታችን ጋር ተያይዘው የመጡ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በየደረጃው በሚገኙ የመንግስት አመራር አካላት ዘንድ በሚታዩ ድክመቶች፣ በተለይ ደግሞ በምግባረ ብልሹነት ምክንያት የተፈጠሩ ችግሮች በወቅቱና በአስተማማኝ ሁኔታ ባለመፈታታቸው የተከሰቱ ናቸው፡፡ የመልካም አስተዳደር ችግሮችም ሆነ የህዝባችንን ተጠቃሚነት በተገቢው ደረጃ ያለማረጋገጥ ድክመት በዋነኛነት የምግባረ ብልሹነት ውጤቶች ናቸው፡፡ ምግባረ ብልሹነት ደግሞ በመንግስት የኃላፊነት ቦታዎች ላይ የተቀመጡ ሰዎች የተረከቡትን ህዝባዊ አደራ ለህብረሰባዊ ለውጥ ማምጫ በትጋት የሚሠሩበትን መሣሪያ ማድረግን እየዘነጉ ስልጣንን የኑሮአቸው መሠረት የማድረግ አተያይና በዚህም ላይ የተመሰረተ ተጨባጭ ስህተት ከመፈፀማቸው ጋር ተያይዞ የተከሰተ ውጤት ነው፡፡ ይህ መታየት በጀመረበት ጊዜ ሁሉ የእድገታችን ፍጥነት መቀነሱም ሆነ የህዝብ ተጠቃሚነት ለአደጋ መጋለጡ አይቀርም፡፡

መላ የአገራችን ህዝቦች በየአካባቢው ሲመለከተው የቆየውን በስልጣን ካላግባብ የመጠቀም ዝንባሌ እና የህዝብ አገልጋይነት መጓደል መነሻ በማድረግ ቅሬታቸውንና የሚታያቸውን የመፍትሄ ሃሳብ እያቀረቡ ሲታገሉ ቆይተዋል፡፡ እነሆ ይህን የህዝብ ትግል መነሻ በማድረግና ጉዳዩን ከልብ በመቀበል መንግስት ባሳለፍነው ዓመት መጨረሻ ራሱን ከዚህ ዝንባሌ ለማፅዳት ቁርጠኛ እንቅስቃሴ ማካሄድ ጀምሯል፡፡ በዚህ እንቅስቃሴ ቀደም ሲል የተጀመረውን አገራዊ ህዳሴ ከመቀዛቀዝ አውጥቶ ወደ ቀጣይ የለውጥ ሂደት ለማሸጋገር አንዱ ቁልፍ እርምጃ መንግስታዊ ስልጣንን ወደ ግል ኑሮ ማሻሻያ ለማሸጋገር የሚደረገውን ይህን ዝንባሌና ጥረት ማስቆምና መንግስት በርግጥም የህዝብና የአገር መገልገያ መሳሪያ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ ለህዝቡም ብቁና ፍትሃዊ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል ማድረግ ነው፡፡

ከዚህ በመነሳት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መደበኛ ስራውን በሚጀምርበት ከፊታችን ባለው ወር ውስጥ የፌዴራል መንግስትን የአመራር ሥርዓት በአዲስ መልክና ቅኝት ለማዋቀር ተግባራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል፡፡ የፌዴራሉ አካል የሆኑ ክልል መንግሥታትም ተመሳሳይ ቅኝት እንደሚከተሉ ይጠበቃል፡፡ በዚህ መሰረት የመንግስት ስልጣንን ካላግባብ የመጠቀም ዝንባሌን የሚገታና ከእንግዲህ በውጤት አልባነት የመንግስት ስልጣን ላይ ተቀምጦ መቆየት የማይቻል መሆኑን የሚያረጋግጥ አዲስ የመንግስት ምክር ቤት የማደራጀት እንቅስቃሴ ይካሄዳል፡፡ በዚህ እንቅስቃሴ የተቻለውን ያክል ብቃትና ቅንነት ያላቸውን ግለሰቦች በኃላፊነት ላይ በማስቀመጥ የመንግስት የስራ አፈፃፀም በውጤትና በውጤት ብቻ የሚመራ እንዲሆን ማድረግ ይጀመራል፡፡ ይህን ተከትሎ ውጤት ያላመጣ ማንኛውም ሰው በማንኛውም ሽፋን በመንግስት ስልጣን ላይ እንደማይቀጥል የሚያረጋግጥ ቋሚ የአሰራር ስርዓት ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

**የተከበራችሁ የህዝብ ተወካዮች እና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች አባላት፣**

**የተከበራችሁ መላ የአገራችን ህዝቦች፣**

ለማንም ግልፅ እንደሚሆነው አገራችን የምትገኝበት የእድገት ደረጃ ከጥልቅ ድህነት ለመውጣት የሚደረግ መፍጨርጨር ያለበት እና በየጊዜው ዉስብስብ ሁኔታዎች የሚከሰቱበት መሆኑ የማያጠያይቅ ቢሆንም ላለፉት 25 ዓመታት እንደተመለከትነው በሁሉም መስፈርቶች ወደፊት ስንራመድ ቆይተናል፡፡ በኢኮኖሚና ማህበራዊ፣ በዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር እንዲሁም በውስጣዊ ሰላምና አለም አቀፍ ግንኙነት መስክ ረጅም ርቀት ተጉዘናል፡፡ በመሆኑም በዚህ መድረክ ከተከሰቱት አጠቃላይ ሁኔታዎች በመነሳት በመላ የአገራችን ህዝቦች ትግልና ጥረት የተመዘገቡ ድሎችን በማስጠበቅ፣ መልካም ጅምሮችን ዳር በማድረስና የህዝባችንን ተጠቃሚነት በማስፋት ማሳካት ይገባናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እድገታችን የወለዳቸው አዳዲስ ተግዳሮቶችን ጨምሮ ከራሳችን የአመራር ድክመት የፈለቁና በአገራችን ፊት የተደቀኑ ችግሮች ደግሞ አስተማማኝ መፍትሔ የሚሹ ሆነው የሚገኙ ናቸው፡፡ እነዚህን ተግዳሮቶች በፈርጅ በፈርጃቸው እየፈቱ መልካሙን ጅምር አጠናክሮ ለማስቀጠል፣ በሁሉም መስክ ሚዛኑ የተጠበቀና ህገ መንግስታዊ ስርዓታችንን በተከተለ አኳኋን የሚካሄድ ትግልን ማጠናከር የግድ ይላል፡፡ ሰላማችንን ለማወክ የሚሹ የውስጥና የውጭ ፀረ-ሰላምና አሸባሪ ሃይሎችን በአስተማማኝ ሁኔታ እየመከትን ነገር ግን ደግሞ ተግዳሮቶችና ችግሮችን በአስተማማኝ ደረጃ ለመፍታት የሚያስችል በህገ-መንግስታዊ መርሆዎቻችን በመመራትና በዚሁም በመገዛት የሚካሄደውን ትግል ማጠናከር ይገባናል፡፡ አገራችን በጠንካራ የኢኮኖሚና የፖለቲካ መሰረት ላይ በተገነባችበት በዚህ ወቅት ህገ-መንግስታዊ ስርዓታችንን አስተማማኝ የለውጥ መሳሪያ አድርገን እስከተጠቀምንበት ድረስ በርግጥም ረጅም በማይባል ጊዜ ያሰብነውን ግብ ማሳካት እንደምንችል እምነቴ የፀና ነው፡፡

**አመሰግናለሁ**